ግብጽ አረብ ሪፐብሊክ ጁማዳ አልአኺራ 11/1443 ሂ.
የአውቃፍ ሚንስቴር ጃንዮሪ 14/2022 ግ.

# ማህበራዊ እሴቶች

ምስጋና ሁሉ በተከበረው መጽሐፉ
ِنَّ اللَّهَ يَأْمُرُ بِالْعَدْلِ وَالْإِحْسَانِ وَإِيتَاءِ ذِي الْقُرْبَى وَيَنْهَى عَنِ الْفَحْشَاءِ وَالْمُنكَرِ وَالْبَغْيِ يَعِظُكُمْ لَعَلَّكُمْ تَذَكَّرُونَ}
ለአለው ለዓለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የአንቀጹዋ ትርጉም፡

(አላህ በማስተካከል፣ በማሳመርም፣ ለዝምድና ባለቤት በመስጠትም ያዛል፡፡ ከአስከፊም (ከማመንዘር)፣ ከሚጠላም ነገር ሁሉ፣ ከመበደልም ይከለክላል፡፡ ትገነዘቡ ዘንድ ይገስጻችኋል፡፡) ማለት ነው፡፡

አጋር የሌለው ብቸኛ አላህ እንጅ የሚገዙት አምላክ እንደሌለ እመስክራለሁ፡፡ ሰይዳችንና ነብያችን ሙሐመድ የእሱ ባሪያና መልእክተኛ በመሆናቸውም እመሰክራለሁ፡፡ ጌታዬ ሆይ! የምህረት እዝነትህን፣ ሰላምህንና በረከትህን በርሳቸው፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸውና እስከ እለተ ቂያማ ድረስ በመልካሙ መንገድ ለተከተሏቸው አውርድ፡፡

ከዚህም በመቀጠል

እሴቶች በማህበረሰባት ሰርጸው መታየታቸው እድገታቸውንና ስልጣኒያቸውን፣ አንድነታቸውን፣ ትስስራቸውንና መረጋጋታቸውን ያንጸባርቃሉ፡፡ በአንፃሩም የማህበረሰባት ወድቀትና ኋላ ቀርነት ያላቸው የማህበራዊ እሴቶች ከምችት በመፈራረሱ ይጀምራል፡፡ በሥነ ምግባር አልባነት የተመሰረተ ማህበረሰብ የመፈራረስ መሰረቱን በውስጡ አቅፎ

ይጓዛል፡፡ ምክንያቱም የቆመው ጠንካራ ባልሆነ መሰረት ነውና፡፡ የሚከተለውን ግጥም የደረሰው ደራሲ እጅግ ይደነቃል፡

የህብረተሰቦች ማንነት ዘላቂ የሚሆነው በሥነ መግባራቸው ነው

ሥነ ምግባራቸው ከተወገደ እነሱም ከመድረ ገጽ ይጠፋሉ፡፡

ወደእውነት ያደላ የሆነው ሃማኖታችን የማህበረሰቡን ማንነት ለሚጠብቀውና መዋቅሩን ለሚያጠናክረው የማህበራዊ እሴት ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው መሆኑ አያጠራጥርም፡፡ ምክንያቱም መልካም እሴቶችንና ሥነ ምግባርን መጠበቅ የዚህ ታላቅ ሃይማኖት ዋልታ ነውና፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (እኔኮ የተላኩት መልካም ሥነ መግባርን ለማሟላት ነው)፡፡

ከነዚህ እሴቶች በቀደምትነት የሚጠቀሰው ጥቅሙ ለመላ ማህበረሰቡ የሆነው መተጋገዝ፣ መተባበርና አብሮ መኖር የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ ሀገር ለመላ ልጆቹዋ ነች፡፡ የእሷም እድገት እውን የሚሆነው የሃይማኖት፣ የቀለምና የጾታ ልዩነት ሳይኖር በነሱ በሁላቸውም ክንድ ነው፡፡ ይህ መርህ ሲረጋገጥ ለኔ ብቻ ባነይት፣ ራስን ማስቀደምና ራስ ወዳድነት ተሰውሮ መሰረቱ ፍቅርና ስጦታ የሆነ የተዋሀድ ማህበረሰብ ለመገንባት የሚያስችለው የሰብአዊ ወንድምነት መርህ ይነግሳል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

{وَتَعَاوَنُوا عَلَى الْبِرِّ وَالتَّقْوَى وَلَا تَعَاوَنُوا عَلَى الْإِثْمِ وَالْعُدْوَانِ}

(በበጎ ነገርና አላህን በመፍራትም ተረዳዱ፡፡ ግን በኃጢአትና ወሰንን በማለፍ አትረዳዱ፡፡) ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (በመዋደዳቸው፣ በመተዛዘናቸውና በመደጋገፋቸው የምእምናን ምሳሌ ከሱ አንድ ክፍል ህመም በሚሰማው ጊዜ ሌሎችም ክፍሎች እንቅልፍ በማጣትና በህመም እንደሚጋሩት አንድ አካል ነው)፡፡ እንድሁም በሌላ ሐዲስ እንድህ ይላሉ፡ (አሽዓርዮች በዘመቻ እያሉ ስንቃቸው ሊያልቅ ሲቃረብ ወይም በመዲናም ሲኖሩ የልጆቻቸው ቀለብ እያነሰ ሲመጣ ያላቸውን ሁሉ በአንድ የተዘረጋ ጨርቅ አከማችተው እንደገና በአንድ መለኪያ እኩል ይካፈሉታል፡፡ እነሱ የኔ ወገኖች ናቸው እኔም የነሱ ወገን ነኝ)፡፡

ሌላው የማህበራዊ እሴት ደግሞ ልኡልነት፣ ጨዋነትና ሌሎችን ማስቀደም የሚለው እሴት ነው፡፡ ይህ እሴት የሀገራዊና ማህበራዊ ትስስርን ያጠናክራል፡፡ ከማህበረሰቡ አባላት መካከልም ፍቀርን፣ ወንድማዊነትንና ልበ ንጹህነትን ያሰርፃል፡፡ ለዚህም ነው ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) የሚከተለውን ምክር ያስተላለፉት፡ (አትመቀኛኙ፣ ለማታለልም ብላችሁ የማትገዙትን እቃ አታሞግሱ፣ አትጠላሉ፣ ጀርባም አትሰጣጡ፣ ከፊላችሁ ሌሎች ሊሸጡ ያሰቡትን ነገር ዋጋ ቀንሼ እሸጥለሃለሁ በማለት አያፋርሱ)፡፡

እንድሁም እንዲህ ይላሉ፡ (የወንድሙን ጉዳይ ያወጣ ሰው አላህ ጉዳዩን ያወጣለታል፡፡ ከአንድ ሙስሊም ጭንቅን ያቃለለ ሰውም አላህ ከትንሳኤ ቀን ጭንቆች አንዱን ያቃልለታል፡፡ አንድን ሙስሊም ከአዋራጅ ነገር የሰወረ ሰው አላህ በትንሳኤ ቀን ከውርደት ይሰውረዋል)፡፡

ሌላው የማህበራዊ እሴት ደግሞ እነሱን መንከባከብ ሃይማኖታዊ፣ ብሄራዊና ሰብአዊ ግዴታ በመሆኑ ታታሪዎችን፣ የሙታን ልጆችን፣ ደካሞችንና አረጋዊያንን የመንከባከብ እሴት ነው፡፡

ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ ( ባሏ የሚተባትና ምስኪንን ለመርዳት ጥረት የሚያደርግ ሰው በአላህ መንገድ ተጋድሎ እንደሚያደርግ ወይም ቀንን በጾምና ሌሊትንም በስግዴት አንዳሳለፈ ሰው ነው፡፡) እንድሁም አንድህ ይላሉ፡ (እናንተ በደካሞቻችሁ እንጂ ድልንና ሲሳይን ታገኛላችሁን) እንዲሁም የእስልምና እምነት የታታሪዎችን ስኬቶች ለማህበረሰቡ ተጨማሪ ኃይል እንደሚሆኑ ያምናል፡፡ ታታሪዎች ለሌሎች አርአያ በመሆናቸው በማህበረሰቡ ሕይወት ውስጥ ተገቢ ሚናቨውን እንዲጫወቱ አድርጓቸዋል፡፡ ከዚህም አንፃር (ከርሳቸው አላህ ይውደድና) አብደላህ ኢብን ኡም መክቱም የነብያችን ሙአዚን ነበሩ፡፡ እንድሁም የመዲና ነዋሪዎችን እንዲያገልግሉና በስግደትም እንዲመሩ ነብያችን ብዙ ጊዜ ሃላፊነት ይሰጧቸው ነበር፡፡

****

ምስጋና ሁሉ ለአለማቱ ጌታ ለአላህ ይገባው፡፡ የእዝነት መህረትና ሰላም የነብያትና የመልክተኞች መደምደሚያ በሆኑት በሰይዳችን ሙሐመድ (ሶ.ዐ.ወ.) በቤተሰቦቻቸውና በመላ ባልደረቦቻቸው ይውረድ፡፡

ከማህበራዊ እሴቶች በጣም ጉልሁ ደግሞ ወሬዎችን ከማነፋስና ከማሰራጨት በፊት የማጣራትና የማረጋገጥ እሴት ነው፡፡ የእስልምና እምነት ለዚህ ክቡር እሴት ልዩ ትኩረት የሰጠ ሲሆን አሉባልታን የማናፈስ አላማ ማህበረሰቡን ከውስጥ በኩል ማዳከም፣ ከነዋሪዎች መካከል ተስፋ መቁረጥና የሽንፈት ስሜት ማሰራጨት በመሆኑ አሉ ባልታ ማነፈስንና አናፋሾችን በጥብቅ አስጥንቅቋል፡፡ አላህ (ሱ.ወ.) እንድህ ይላል፡

يَا أَيُّهَا الَّذِينَ آمَنُوا إِنْ جَاءَكُمْ فَاسِقٌ بِنَبَإٍ فَتَبَيَّنُوا أَنْ تُصِيبُوا قَوْمًا بِجَهَالَةٍ فَتُصْبِحُوا عَلَىٰ مَا فَعَلْتُمْ نَادِمِينَ}

(እላንተ ያመናችሁ ሆይ! ነገረኛ ወሬን ቢያመጣላችሁ በስህተት ላይ ኾናችሁ ሕዝቦችን እንዳትጎዱና በሠራችሁት ነገር ላይ ተጸጻቾች እንዳትኾኑ አረጋግጡ፡፡) ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) አንድህ ይላሉ፡ (አንድ ሰው ለመዋሸቱ የሰማውን ሁሉ ማውራቱ በቂው ነው)፡፡ ልባም ሰው ቃል ከመሰንዘሩ በፊት ያስባል፡፡ ደደብ ሰው ደግሞ ምንም ያለ ማሰብ ቃሉን ይሰነዝራል፡፡ ነብያችን (ሶ.ዐ.ወ.) እንድህ ይላሉ፡ (በአላህና በመጨረሻይቱም ቀን የሚያምን ሰው ደግን ነገር ይናገር ወይም ዝም ይበል)፡፡

እኛ ከመላ የማህበረሰቡ ነዋሪዎች መካከል መላመድና ትስስር እንዲረጋገጥ ማህበራዊ እሴቶችን አጥብቀን መያዝ ያስፈልገናል፡፡

ጌታችን ሆይ! ወደመልካም ምግባር ምራን፡፡ ለመልካም ምግባር አንተ እንጅ ማነም ሊመራ አይችልምና፡፡ አሚን፡፡